# የአቋም መግለጫ

## የአቶ ስዬ አብርሃና የቤተሰቦቻቸው ክስ ለመጨረሻ ውሳኔ ስለመቀጠሩ

በሰሜን አሜሪካና በካናዳ የምንኖር የትግራይ ተወላጆች የአቶ ስዬ አብርሃንና የቤተሰቦቻቸውን የክስ ሂደት በአትኩሮት የምንከታተለው ጉዳይ በመሆኑ፣ ከዚህ የአቋም መግለጫ ጋር በአባሪነት የተያያዘውንና ስለሕገመንግስት መከበርና ስለፍትህ አቤት የሚለውን ደብዳቤ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም ለኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ለተከበሩ አቶ መለስ ዜናዊ፣ በቅጂም ለሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላትና ለተከበሩት የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች፣ እንዲሁም ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም በተወካዮቻችን አማካይነት ለተከበሩ ዶ/ር ሳሙኤል አሰፋ በሰሜን አሜሪካ የኢፌዲሪ መንግስት ባለሙሉሥልጣን አምባሳደር ማቅረባችንን እናስታውሳለን።

ይህንን ክስ አስመልክቶም ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት በዋለው ችሎት በሰብሳቢ ዳኛ በተከበሩ አቶ ፍስሃ ወርቅነህ ዳኝነት ተከሳሾች ጠበቆችና የፀረሙስና ኮሚሽን ተወካይ በተገኙበት እንደተገለፀው፣ ለመጨረሻ ውሳኔ ተለዋጭ አጭር ቀጠሮ በማስፈለጉ በመዝገብ ቁጥር 7366 የቀረበው የአቶ ስዬ አብርሃ ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም (June 22, 2007)፣ እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 9087 የቀረበው አቶ አሰፋ አብርሃና የሌሎች ሶስት ተከሳሾች ጉዳይ በተመሳሳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም (June 29, 2007) መቀጠሩን ተመልክተናል።

ምንም እንኳን የእነዚህ ክሶች የፍትህ ሂደት እጅጉኑ የተራዘመ የተጓተተና ኢፍትሃዊ አፈፃፀም ጎልቶ የታየበት ቢሆንም፣ ለመጨረሻ ውሳኔ በመቀጠሩ በበጎ ገፅታ እንድንመለከተው አስችሎናል። በሰብሳቢ ዳኛ በተከበሩ አቶ ፍስሃ ወርቅነህ የተገለፀው የመጨረሻ ውሳኔ ሂደት ተግባራዊ ሆኖ ጉዳዩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚዘጋም ተስፋ እናደርጋለን።

በዚህ በአቶ ስዬ አብርሃና በቤተሰቦቻቸው የክስ ማዕቀፍ ውስጥ ግራ ቀኙን አነጋጋሪና አወዛጋቢ ሆኖ ለስድስት ዓመታት የተጓተተው ይህ ክስ በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈና ያልተረጋገጠ በመሆኑ፣ አቶ ስዬ አብርሃና ቤተሰቦቻቸው መብታቸው ተከብሮ በነፃ ምንደሚለቀቁም እንጠብቃለን።

በሰሜን አሜሪካና በካናዳ የትግራይ ተወላጆች
Email: Justice4siye@Gmail.com

<u>በአባሪነት የተያያዘውን የፍትህ አቤቱታ ይመልከቱ</u>

ግንቦት 21 ቀን 1999

ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ
የኢፌዲሪ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር
አዲስ አበባ

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣

በሰሜን አሜሪካና በካናዳ የምንኖር የትግራይ ተወላጆች የአገራችንን የፍትህ ሥርዓት በማስመልከት በተለይም የአቶ ስዬ አብርሃንና የቤተሰቦቻቸውን ጉዳይ እንደመነሻ ነጥብ በመያዝ ተከታታይ ሕዝባዊ ውይይቶችን በማካሄድ የደረስንበትን መደምደሚያና ሕዝባዊ አቤቱታችንን ለክቡርነትዎና ለፍትህ አስፈፃሚ ኣካላት ስናቀርብ፣ የኢፌዲሪን ሕገመንግሥትና የአገሪቱን ሕግ መሰረት ያደረገ ፍትሃዊ ውሳኔን በመጠበቅ ነው።

የኢፌዲሪን ሕገመንግሥት ከማክበርና ከማስከበር ብሎም የአገሪቱን ሕግ ከማስፈፀም አኳያ በአቶ ስዬ አብርሃና በቤተሰቦቻቸው የፍትህ ሂደት ላይ በዳኝነት አለመሟላት እየተመካኘ እየተፈፀመ የሚታየው የተራዘመና የተጓተተ የፍትህ አካሄድ፣ ዋስትና ለመከልከል የወጣ አዲስ ሕግ፣ የተወሰኑ የመከላከያ ምስክሮች እንዳይሰሙ መከልከል፣ በተለየ ሁኔታ ለይቶ ማሰር፣ እና የመሳሰሉት አፈፃፀሞች ለበርካታ የኢፍትሃዊነት እንድምታዎች አመላካች ሆነው አግኝተናቸዋል። እነዚህም አፈፃፀሞች የሕጐች ሁሉ የበላይ የሆነው የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ስለዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ ካስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጩና የአንድን ዜጋ ፍትህ የማግኘት ሕገመንግሥታዊ መብት የሚነፍጉ ናቸው እንላለን።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣

የአቶ ስዬ አብርሃና የቤተሰቦቻቸው ጉዳይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባስገረመ አኳኋንና በማንኛውም መመዘኛ ፍትሃዊነቱን ሊያረጋግጥ የማይችል ይልቁንም በማያሻማ መልኩ ኢፍትሃዊና ኢሕገመንግሥታዊ አካሄድ ሆኖ አግኝተነዋል። ይኸውም በበቂ ማስረጃ ባልተደገፈና ባለተረጋገጠ ክስ፣ ሕጉ በሚያዘው መሰረት ዳኞች እንኳን ተሟልተው ባልተሰየሙበት የፍርድ ሂደት፣ የሕግ ከለላ መብትን በመንፈግ፣ ጥፋተኝነታቸው ያልተረጋገጠ ዜጎችን ለዓመታት በእስራት መቅጣት፣ በኢትዮጵያ ሕዝቦች የተባበረ ተጋድሎና መራራ መስዋእትነት እውን የሆነውን የኢፌዲሪን ሕገመንግሥት የጣሰ ኢፍትሃዊ አካሄድ ከመሆኑም በተጓዳኝ የፍትህ

ስርዓቱን ርትዓዊነትና የፍትህ አስፈፃሚ አካላትን ሕገመንግስታዊ ነፃነት እንድናጠያይቅ አስገድዶናል።

ይህም የፍትህ አፈፃፀም ሂደት አንድም የፍትህ አስፈፃሚ ኣካላት በሕገመንግስቱና በሕዝብ የተጣለባቸውን መብት ግዴታና አደራ አለመወጣታቸውን፣ አልያም የመንግስት አስፈፃሚ ኣካላት ሕገመንግስቱን በመጣስ ከሕግ በላይ በመሆን በፍትህ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ ጣልቃ በመግባት ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት እንዳያከናውኑ አግደዋቸዋል፣ ወደሚሉ የኢፍትሃዊነት መገለጫ ወደሆኑ መደምደሚያዎች አድርሶናል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣

በመሆኑም ነው፣ ክቡርነትዎና የፍትህ አስፈፃሚው ኣካላት ሕገመንግስቱንና የአገሪቱን የፍትህ ስርዓት በግንባር ቀደምትነት ከማክበርና ከማስከበር አኳያ ካለባችሁ ከፍተኛ ኃላፊነትና ግዴታ በመነሳት፣ ይህንን በማንኛውም መመዘኛ በፍትሃዊነት ሊፈረጅ ያልቻለውን የአቶ ስዬ አብርሃንና የቤተሰቦቻቸውን እስራትና መጉላላት ከሕገመንግስቱና ከሕግ አኳያ ተመልክታችሁ መብታቸው ተከብሮ በነፃ እንዲለቀቁ በአፅንዖት የምንጠይቀው።

የተከበሩት የኢፌዲሪ የፌዴሬሽንና የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤቶች ሕግ አውጭና ሕግ መወሰኛ ብቻ ሳይሆኑ አስፈፃሚው አካል ሕገመንግስቱን በማክበርና ፍትህን በማስፈን ሂደት ውስጥ የሚፈፅማቸው ግድፈቶችንና ጥሰቶችን ለመመልከት ካለባቸው ግዴታና አደራ አኳያ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ስለዜጎች መብት መከበር ካለበት ሕገመንግስታዊ ግዴታ በመነሳት የዚህ ሕዝባዊ አቤቱታ ቅጂ እንዲደርሳቸው አድርገናል።

ከሰላምታ ጋር

በሰሜን አሜሪካና በካናዳ የትግራይ ተወላጆች
Email: justice4siye@Gmail.com

ለኢፌዲሪ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ለአቶ መለስ ዜናዊ
በፋክስ ግንቦት 21 እና በድጋሚ ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

<u>ቅጂ፣</u>

- ለተከበሩ አቶ ከማል በድሪ
  የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዝዳንት
  በፋክስ ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
  የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ም/ፕሬዝዳንት
  በፋክስ ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ አቶ ስዩም መስፍን
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር
  በፋክስ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አፈጉባኤ
  በፋክስ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለክብርት ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ም/አፈጉባኤ
  በፋክስ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ አቶ ደግፌ ቡላ
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽ ምክርቤት አፈጉባኤ
  በፋክስ ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ አቶ መሐመድ ሰርሃዬ
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽ ምክርቤት ም/አፈጉባኤ
  በፋክስ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ ዶ/ር ካሣ ገብረህይወት
  በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር
  በፋክስ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ አቶ አስመላሽ ወልደስላሴ
  በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት
  የሕግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር
  በፋክስ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

- ለተከበሩ አቶ ፋንታዬ ገዛኸኝ
  በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት
  የሕግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ም/ሊቀመንበር
  በፋክስ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
  <u>አዲስ አበባ</u>

- ለተከበሩ ዶ/ር ሳሙኤል አሰፋ
  በአሜሪካ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር
  በአካል በተወካዮቻችን እንዲደርሳቸው ተደርጓል
  <u>ዋሽንግተን ዲሲ</u>